# "ለአይቀሬው የህዝብ ድል ህዝባዊው ማዕበል፤ ህወሃት ወያኔ/ኢህአዴግ/ን የማስወገጃ የመጨረሻው ምዕራፍ"!

በ2008 አጋማሽ ጀምሮ አሁንም የቀጠለው ህዝባዊ ማዕበል የህወኃት/ኢህአዴግን የሻገተ ስርዓት በማንኮታኮት ላይ ይገኛል። ከስርዓቱ ገዥዎች አንደበት እንደምንሰማው እና በተጨባጭም እንደምናየው የህወሃት ወያኔ ድርጅታዊ ሁለገብ አቅሞች ዳግም በማያንሰራሩበት ሁኔታ በኃያሉ የህዝብ ክንድ ተደቁሰዋል። በሁሉም የአገራችን ክፍል ሊባል በሚያስችል ሁኔታ እየተካሄደ ያለው ህዝባዊ ማዕበል የስርዓቱን ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችና የፀጥታ መዋቅሮች ላይ ትኩረት አድርጎ እየተወሰዱ ባሉ እርምጃወች የህወኃት ድርጅታዊ አቅሞች ብቻ ሳይሆኑ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ የሚገኙ ጥገኛ የጥቅም ተጋሮቹና ወዳጆቹም አብረው ተደቁሰዋል።

ይህ የህወሃት ወያኔ ገዥወችና ወዳጆቻቸው ያልጠበቁት የህዝብ አብዮት እጅጉን እንዳስጨነቃቸውና ሂደቱም እንደጠበባቸው በቅርበት እያየናቸው ነው። ከአገር ውጭና በአገር ውስጥም የሚገኙ የጥቅም ወዳጆቻቸው ሳይቀሩ ጭንቀታቸውንና ስጋታቸውን በአደባባይ አውጥተው ሲናገሩ እየሰማን ነው፤ ነገር ዓለሙ አልቁአልና የህዝብ ጥያቄ መልስ ካልሆነ ውርደትህ የከፋ ይሆናል ሲሉ ሲመክሩም ሲማፀኑም ከርመዋል። የነዚህ መካሪ ኃይሎች ምክር ምንም እንኳአን መነሻቸው ከህወኃት/ኢህአዴግ የተያያዘው የግል ጥቅማቸው ቢሆንም የሰማዩን የደመና ክብደት በማየት አይቀሬውን የህዝብ ድል በመረዳታቸው ጠቃሚ ምክር ነበር።

ከህወሃት ወያኔ/ኢህአዴግ መንደርም እንደሰማነው፤ ይህ ህዝባዊ ማዕበል ወደ ኃላ እንደማይታጠፍና ጎርፍ ሁኖ ጠራርጎ እንደሚወስዳቸው ስጋታቸውን በመግለፅ የወዳጆቻቸው ምክር ተግባራዊ እንዲደረግ ሃሳብ ያነሱና ብዙም የተነጋገሩበት ሁኔታ እንደነበር ተሰምቷል።

በርግጥም በዚህ የህዝብ ማዕበል ንቅናቄ የህወሃት ወያኔ/ኢህአዴግ ግፈኞች ሁለት አማራጮች ከፊታቸው ተደቅነውላቸው ነበር፤

1. የማይቀለበሰውን የህዝብ የንቅናቄ ማዕበል ነባራዊ ሁኔታ በመመልከትና የወዳጆቻቸውንም ምክሮች በመስማት የህዝብ የሙብት ጥያቄ ሰላማዊ መልስ መስጠት፣ ለፍታዊና ለዴምክራሲያዊ ስርዓት ምስረታ ዝግጁ መሆን። (የተሻለ አማራጭ)

2. ሁሉንም የህዝብ ጥያቄ በኃይል መጨፍለቅ፤ ይህ አማራጭ በተለይም እየታየ ባለው የአገራችን በማይቀለበሰው የህዝብ ንቅናቄ ላይ ተግባራዊ ለማድረግ እጅግ ከባድ ዋጋ ያስከፍላል። ለገዥወቹም ቢሆን ብዙ ገንዘብ ያስከሰክሳል፤ ማንኛውም ዓይነት የኢኮኖሚ እንቅስቃሲ ያስቆማል፤ የልማት አውታሮችን ያወድማል፤ የገዥወቹን መንደርም ይከፋፍላል፤ ገዝወቹ በሚፈፅሙት ግፍና በደል ህዝቡ ይበልጥ ለነፃነቱና ለበቀል በነፍስ ወከፍ ይነሳል።(መጥፎ አማራጭ)

የህወሃት ወያኔ/ኢህአዴግ ደካማነት ታጥቦ የማይለቅ መርዝ ሁለተኛውን መጥፎ አማራጭ መርጧል። ይህ ማለት በመላ አገሪቱ የተነሳውን ህዝባዊ ጥያቄ ለመመለስ ፈቃደኛ አለመሆኑን አረጋግጡአል። እየተካሄደ ባለው ህዝባዊ አብዮትም የፈሰሰው ደም እና የወደመው ንብረት ይበቃል ከማለት ይልቅ እንደገና እጥፍቶ ለመጥፋት ተዘጋጅቷል።

ይህ በትግሬ ወያኔ ስር የወደቀን አገር እና ህዝብ፤ አሁንም ለዳግም ጥፋት ይረዳኛል ብሎ ያሰበውን የአፈናና የጭፍጨፋ አዋጅ በግልፅ አውጇል። ይህ ፀረ-ህዝብ የጭፍጨፋ አዋጅ መላ ህዝቡን ይበልጥ ለጎርፍ የሚያነሳሳ እንጅ መሬት የሚነካ ነገር አይደለም።

አዋጅ የተወሰነን ቡድን ለማንበርከክ ሊሰራ ይችል ይሆናል፤ አሁን ባለው ሁኔታ ግን የኢትዮጵያን ህዝብ በአዋጅ ማሸነፍ ቅዠት ነው። ከመሰረቱ ህወኃት/ ኢህአዴግ የሚባል ድርጅት ዘረኛ፤ ገዳይ፤ ዘራፊ፤ ገንጣይ አስገንጣይ ወንጀለኛ ድርጅት ስለሆነ ምንም ህጋዊነት የለውም። በመሆኑ ይህ ደመኛ የአገር ጠላት የሚያወጣቸው ህግ-ነክ ሆነ ሌሎች ጉዳዮች ውድቅ ናቸው።ህወሃት ወያኔ አይገዛንም፤ እያልን ከዚህ ወራዳ ድርጅት የተያያዘ ሁሉ ለኢትዮጵያ ህዝብ አይሰራም ።

እርግጥ ነው እስካሁንም የምንታገለው የማንነት ሙብታችን እና ብሄራዊ ጥቅማችን ከአንድ ሰፈር በተሰባሰቡ ዘረኞች እጅ በመግባቱና እንደ ዜጋም ባገራችን መኖር ስላልቻልን ነው፤ አሁን ደሞ ህወሃት ወያኔ ይህንን ጭፍጨፋ በይፋ በሰነድ አፅድቀው መምጣታቸው እኛ ጭቁን ኢትዮጵያውያንን የበለጠ አንድ ሁነን እንድንነሳ ያደርገናል።

በአሁኑ ሰዓት ህወሃት ወያኔ/ኢህአዴግ ከውድቀት ራሱን ለመታደግ ሁሉንም አቅሙን አሟጦ በመጠቀም፤ የመጨረሻ መፍጨርጨር በማድረግ ላይ መሆኑን በግልፅ እያየን ነው። ህወሃት ወያኔ/ኢህአዴግ የተባብረ የህዝብ ትግል ፍጥነቱ እና ውጤታማነቱ ወገቡን ስለቆረጠው ባዶነቱን አውቆታል፤ ከዚህ "እኔ ከሞትኩ ሳር አይብቀል እንዳለችው እንሰሳ" ያወጣው የገደብ አዋጅም የራሱን የጫካ ህገ-መንግስት አፈር ከማብላቱም በላይ የአለማቀፍ ህጎችንና መርሆችን በአደባባይ ጥሷል። እኛም የጭቆናው ገፈት ቀማሾች እየገደለን፣ እያሰደደን፣እየዘረፈን፣ማንነታችን እየቀማን ያለተንጅወች ኢትዮጵያውያን ለዓላማችን ስኬት፣ ለህዝባችን ነፃነትና ለአገራችን ክብር ስንል ሙሉ አቅማችን አቀናጅተን ይህንን ወራዳ ስርዓት ቀብሩን ማፍጠን ይገባል። ለዚህም ሁሉም ኃይሎች ልዩነቶታቸውን አስቀምጠው በጋራ

ጉዳዮቻቸው ላይ አንድ ሁነው መነሳት ያስፈልጋል። ህወሃት ወያኔ/ኢህአዴግ የማይወዷትን፣የማያከብሯትን ኢትዮጵያን  ስሟን እየጠሩ መደበቂያ አድርገዋታል !!!

Gabriel Bezuneh.